# ይድረስ ለትግራይ ሕዝብ, ለትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች በሙሉ [ተፈራ አበበ]

February 2, 2018



**የቅሬታ ና የነቀፌታ የተመለሱም ጥሪ**

በመሰረቱ የአንድ ጎሳ ዋና መገለጫው ሀገሩ ነው። ሀገር ማለት የምኖርብት, የምንሰራብት, የምንከበርበት, የማንነታችን መገለጫ, ጥበቃና የሰላም ዋስትና የምናገኝበት, ድንበር ወሰኑ, ወንዙ, መልከዓ ምድሩ, ሁሉም ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ዋናው ሀገር ማለት ሕዝቡ ነው። የሀገር ትምክህቱ ና ኩራቱ ስንልም ራሱ ሕዝቡና ያለውን የሕዝቡን ግንኙነት ነው። ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ ዛሬ እናንተ እንደፈለጋችሁ ወደ ውጭ ሀገራት መውጣት መግባት(ማስወጣት ማስገባት ሉዩ ልዩ ዕቃዎችን ጨምሮ) ስለቻላችሁ, ልጆቻችሁንም በሀገር ውስጥ ሆነ በውጭ ሀገራት እንደልባችሁ ማስተማር ስለቻላችሁ ብቻ። ነገር ግን የተቀረው የሀገሪቱ ሕፃናት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩት ወላጅ ልጆቹን የሚመግበው አጥቶ ልጆች በረሓብ ምክንያት ትምህርት ቤት መሄድ አቅቶአቸው በተባበሩት መንግስታ በሀገር ውስጥ ሲረዱ ብዙ ሕፃናትም ረሓቡ አቅቶአቸው ትምሕርታቸውን ሲአቃርጡ ወላጆችም ተስፋ ሲቆርጡ ትምህርት ቤቶችም በየቦታው ሲሰዘጉ ትውልድም ሲጠፋና ሲበላሽ። ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ ይህንን አላየንም አልሰማንም ነው። በጣም አፈርንባችሁ አዘንባችሁ ይሄ ከትግሬ ከቆየ የህዝብ ማንነት ባህል ና ታሪክ ጋር ፈፅሞ አብሮ አይሄድም ፡ ይሄ ለናሙና ያህል ቀረበ እንጂ የሕዋት መንግስት በትግራይ ሕዝብ ስም የሚሰራው ና የሚአደርሰው ግፍ ሰቆቃ እስራት ግድያ አፈና  ዘረፋ ለመዘርዘር አይደለም። እንዲያው በአጭሩ ለመጥቀስ ያህል

1. የኦሮሞ እናት ልጆ በአጋዚ ጥይት ተገድሎ የልጃ ሬሳ ላይ ተቀመጭ ስትባል
2. የአኝዋክ እናት በጀርባዋ ላይ ካዘለችው ልጃ ጋር አብራ በአጋዚ ጥይት ስትገደል
3. ከ 1.5 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የአማራ, የኦሮሞ, የሱማሌ ተወላጆች ከዚህ ውስጥ ሕፃናት ብቻ 120,000 ሺህ ከየመኖሪያ ስፍራቸው ተፈናቅለው በገዛ ሀገራቸው ውስጥ ሲሰደዱ, ሲራቡ, ሲጠሙ, ጎዳና ሲጣሉ, ሲለምኑ
4. በብዙ መቶዎች ሕዝብ በአደባባይ በአጋዚ ጥይት ሕፃን ሽማግሌ ሴት ወንድ ሳይል ሲገደሉ
5. የአማራ ተወላጆች በመሆናቸው ብቻ መግቢያ መድረሻ ሲያጡ, በየስር ቤቱ በከፋ ጭካኔ ሲደበደቡ, ሲስቃዩ, ወንዶች ብልቶቻቸው ሲኮላሹ, ሴቶች በሴትነታቸው ሲደፈሩ, የአማራ ሴት ልጅ እንዳትወልድ መርፌ በመውጋት መሃን ስትደረግ

6. የኦሮሞ ወጣቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በየስር ቤቱ ሲጣሉ, በከፋም ጭካኔም ሲደበደቡ, ሲስቃዩ, በውሻ መርዝም ሲገደሉ
7. በየማሕበራዊ መገናኛ ሚድያ, በዜና አውታሮች, በስላማዊ ሰልፎች ሁሉ እባካችሁ ልጆቻችሁ ልጆቻንን አይግደሉብን እየተባለ ስትለመኑ ስትጠየቁ
8. የሕዋት መንግስት የሀገሩን መሬት ለባእድ ሀገር ለሱዳን ለመስጠት ሲስማማ

ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ ይህን አላየንም አልሰማንም ነው። ይሄ በአጭር ጊዜ በመጣው ማለትም ክትግራይ ሕዝብ ና ከትግራይ ተወላጆች ከሆነው በትግራይ ሕዝብ ስም በሚነግደው በሕዋት ፓርቲ የተፈፀመ እውነት ና ሃቅ ነው። ስለዚህ ሁላችን የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ ይህን እያያችሁና እየሰማችሁ ዝም በማለታችሁ እጅግ አፈርንባችሁ, አዘንባችሁ, ተቀየምናችሁ, ተቆጣንባችሁ። ዛሬ ተመለሱ በቃ በሉ ለሕዋት። ዛሬም በመመለስ ማስተካከል ይቻላል የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር ባይና ጨዋ ሕዝብ ነው፡ ምክንያቱም እንደ አንድ ሀገር ያለን የረዥም ጊዜ የታሪክ, የአንድነት ግንኙነት ና መዋሃድ  በቀላሉ ስለማይበጠስ ነው። ስለዚህ ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ ለረዥም ጊዜ የነበረውን የትግሬ ሕዝብ ታሪክ ማለት በትንሹ የ3,500 አመት የኢትዮጵያዊነት ታሪክን ሃምሳ አመት ባልሞላው በሕዋት ታሪክ አታርክሱት አትጣሉት። ተመለሱ ይህንንም ጥሪ ስሙ።

ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ የሕዋት መንግስት በገዛበት በ27 ዓመት ውስጥ ያየነው የሰማነው የተደረገው እየተደረገም ያለው ሁሉ

1. ሕዝቡን መከፋፈል ና ለዘመናት የነበሩንን አብሮ መብላት ና መካፈል, ማግኘት ና ማጣት, መደሰት ና ማዘን ዕሴቶቻችን ማጥፋት ነው። የሕዋት ፓርቲ በተቃራኒው መስራትን ዓላማዬ ብሎ የተያያዘ መንግስት ነው። ለናሙና ያህል ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ሆና ሳለ ሕዋት ግን እኛን በትንንሽ ክልሎች በመከፋፈል ትልቅን ኢትዮጵያ እንዳናይና እንዳናስብ አድርጓል እያደርገም ይገኛል። ከዚህም ዓልፎ እርስ በርሳችን በጠላትነት እንድንተያይ ሕዋት ሌት ተቀን ይሰራል የአማራውን ሕዝብ ከኣኦሮሞ ወገኑ ሕዝብ ጋር በማጣላት በማጋጨት አልፎም ሓውልት በማቆም, የሱማሌ ሕዝብን ከኣኦሮሞ ወገኑ ሕዝብ ጋር ማጋጨት, በዚህ ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያኖች ሞት ና ስደት ደረሰባቸው። ዛሬ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የነበረው የእምነት አንድነት በሕዋት ተከፍሎ አብሮ ማምለክ ሆነ ባዓላትን ማክበር የለም, በእስልምና እምነት ተከታዮችም ዘንድ ያለው ችግር በሕዋት የተፈጠረ ነው። በዚህ ውስጥ ይህን እንቢ ያሉና የተቃወሙ ኢትዮጵያኖች የደረሰባቸው እስር, ሰቆቃ, ና ግድያ ነው። ዛሬ ሕዋት ከወሎ ከሚወጣ የአልምዝ እንቁ ማእድን ሽያጭ ገቢ, ከሽኪሶ ከሚወጣ ወርቅ ና የከሰል ድንጋ ሽያጭ ገቢ ሁሉ ሕዋት ብቻ ተጠቃሚ ነው። ነገር ግን በዚህ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ  ከአካባቢው ባዶውን ይፈናቀላል, ይገድላል, ይታሰራል። ሚስኪኑ የአኝዋክ, የጋምቤላ ሕዝብ መሬቱን ተነጥቆ ለባእዳን ሰዎች ና ለሕውሓት አባላቱ በነፃ ሲታደል መሬቱን የተቀማውን ሕዝብ ግን ሕዋት ሲገደል, ሲአስሰር, ባዶውን ሲባረር። ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ ይህ በድፍን ትግራይ ሕዝብ ስም በሕዋት የተሰራ ና የሚሰራ ስራ ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይመጥነንም።  ስለዚህ ሁላችሁ የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ ከሕዋት መንገድ ተመለሱ ብለን ጥሪ እናቀርብላችሃለን።

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ፍፁም አምባገነናዊነት, ግትርነት, ና ወታደራዊ አገዛዝ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ እንደ እንድ ሀገር ሊኖረን የሚጋባውን የጋራ የሆነ ራዕይ ዓላማም አሳጥቶናል, የሀገር ባለቢትነት ስሜት ጭምር እንዳይኖረን አድርሻናል። ስለዚህ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውይን ለከፋ መከራ ሰቆቃ ስደት እራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። የሕዋት መንግስት በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ሕዝብ አደባባይ ድረስ ወጥቶ መብቱን, ችግሩን ቢጠይቅም የሕዋት መልሱ ግን ግድያ, እስር, ና አፈና ብቻ ነው። ውድ የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ አሁን አላየንም አልሰማንም ሳትሉ ከሕዋት ጋር ተባብሮ መቀጠልን አቁሙና ተመለሱ።

3. የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይቆም የማድረግ ና የመነጠል ስራ ነው። ይህም ሕዋት ከሌለ የትግራይ ሕዝብ ህልውና እንደማይኖር አድርጎ በማቅረብ ነው። እውነቱ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ በየቦታው የሚቃወመው የሕዋት ፓርቲ መንግስት እንጂ ፈፅሞ የትግራይን ሕዝብ ሆኖ አያውቅም። በአሁኑ ወቅትም ብቸኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት የሕዋት ፓርቲ መሆኑን ሙሉው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል። ስለሆነም ዛሬ ሕዝቡ በሚአደርገው ሕዋትን ተቃውሞ ሁሉ የሚአጠቃው የሕዋትን ተባባሪዎች, ሰላዮች, ና ባለ ስልጣኖች ነው። ስለዚህ ሁላችሁ የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ ከዝህ ከሕዋት ወጥመድ ፈጥናችሁ ትወጡ ና ትመለሱም ዘንድ ይህ ጥሪ ቀርቦላችሃል።

4. የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ የቤሕራዊ መግባቢያ ቓንቓ እንዳይኖረው ማለትም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመላ ሀገሪቱ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ እንዳይሰራ እንዳይኖር ሁሉም በራሱ ቓንቓ ና ክልል እንዲወሰንና ቤሕራዊ መግባባት እንዳይኖረን ማድረግ ነው። ስለዚህ ሁላችሁ የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ ይህ እጅግ ከሚአሳፍር, ከሚአሳዝን, ከሚአቆጣ የሕዋት ስራ ትመለሱም ዘንድ ይህ ጥሪ ቀርቦላችሃል።

5. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝቅ ብሎ በጎሳው ማንነት እራሱን እንዲግልፅ እንጂ ለዘመናት የነበረውን የኢትዮጵያዊ ማንነቱን, ኩራቱን እንዲተው ተደርሻል እየተደረገም ነው። ይህ ደግሞ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ማንነታች ጋር ይቃረናል ምክንያቱም በጋራ የመጡብንን ጠላቶቻችንን መክተናል, በጋራ ለእንዲት ሀገር ብለን ሞተናል, በጋራ አንዲትን ሀገርን ወክለን ለዘመናት በዓለም ፊት ቆመናል። ስለዚህ ሁላችሁ የትግሬ እናቶች, እባቶች, ሙሕሮች, ወጣቶች, አዛውንቶች, በሃገር ውስጥ, በውጭ ሀገሮች ያላችሁ ሁሉ ይህን እጅግ ክፉ የሆነ ና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የዓባቶቻችን ና የእነቶቻችን ታሪክ ና ተጋድሎ ከሚአጠፍው የሕዋት ስራ ሁሉ ትመለሱም ዘንድ ይህ ጥሪ ቀርቦላችሃል።

ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ እኛማ ሕዋት አመንን, ወደ አዲስ አበባ ሲገባ ከአንግዲህ ሰላም ነው በቃ ሲለን የጦር መሳሪያውንም, ታንኩንም, መድፉንም እግራችው ስር ጥለን አስረከብናቸው, ሕዋት

ትንሽም ቆይቶ (1997) አሁን ዲሞክራሲ ነው ምረጡ ሲለን እሺ ብለን መረጥን መልሱ ግን ከሕዋት በአደባባይ በጥይት መግደልና ማሰር ሆነ፡ እኛማ አመንን ሕዋት ፍትሕ አለ ብለን በየፍርድቤቱ ተንከራተትን በሃሰት ክስ, ያለሰሚ, ያለውንጀል ተከሰስን, ተፈረድብን, ታስረን ተደበደብን, ተገረፍን, ሰቆቃም ተፈፅሙብን። ይህንን ሁሉ አላየንም አልሰማንም እንዳትሉ። ዛሬም እኛ የሕዋት ፓሪቲ እንኳን ለመላው ኢትዮጵያ የትግራይን ሕዝብ ክልል አይመጥንም እንላለን። አሁንም ቢሆን በንፁህ ኢትዮጵያውያን በሆኑት የትግራይ አባቶቻችንና እናቶቻችን ታሪክ, ስራ ና ገድል, የትግራይን ሕዝብ ትልቅነት ሽንጣችንን ገትረን እንከራከራለን። ዛሬም ቢሆን በመመለስ ማስተካከል ይቻላል ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር ባይና ጨዋ ሕዝብ ነው። አስቲ እንግዲህ እናንተም አሳዩን  ሕዋትን መተባብርን ተው, ከዝምታም ውጡና ሕዋትን በአዳባባይ ተቃወሙ, የሕዋትን መንገድ ከመከተል ተመለሱ, አሁንኑ አቁም በቃ በሉት ለሕዋት። ይህንንም ጥሪ ስሙ።

ውድ የትግራይ ሕዝብ, የትግራይ ተወላጆች ና ደጋፊዎች ሆይ የሕዋት መንግስት ኢትዮጵያን በገዛበት በ27 ዓመት ውስጥ ሁሉ በአብዛኛው በትግራ ሕዝብ ና ተወላጆች ዘንድ ያየነው የሕዋት ተባባሪነት ና ፈፁም የሚአስገርም በጣምም በበዛው ዝምታችሁ በእውነት በጣም ተጎዳንባችሁ, አፈርንባችሁ, አዘንባችሁ። ይህም ዓይነቱ አካሄድ የትግራይን ሕዝብ ከቆየ የህዝብ ማንነቱ, ከኢትዮጵያዊ ጨዋነቱ, ባህሉ ና ታሪኩ ጋር ፈፅሞ አብሮ አይሄድም አይመጥነውምም። ስለዚህ የረዥም ጊዜ የትግራይን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱ ና ታሪኩን ሃምሳ አመት ባልሞላው በሕዋት ታሪክ አንዳታረክሱት, እንዳታጉዱፉት,  እንዳትጥሉት, እንዳታጠፉትም ከዚህም ታሪካዊ ተጠያቂነት, ተወቃሽነት ና ነቀፌታ አሁኑኑ ከሕዋት ስራ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ትወጡ, ታቆሙ,  ትመለሱም, ትለዩም ዘንድ እጅግ በታላቅ ትህትናና አክብሮት እስካዛሬም ለዚች አንዲት ኢትዮጵያ ብለው ንፁህ ደማቸውን ባፈሰሱ አጥንታቸውንም በከሰከሱ ንፅህ የትግራይ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ስም አናቀርብላችኋለን።